# በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወኪል ቅርንጫፎች በኩል የሚገዛውን ወርቅ በተመለከተ የተደረገ የዋጋ ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር ከማዳ 3/2015

## 1. መግቢያ

በባህላዊ የወርቅ ምርት ዘርፍ በሚስተዋሉ በርካታ ችግሮች ምክንያት አገሪቱ ማግኘት የነበረባት የውጭ ምንዛሪ እና ሌሎች ከዘርፉ የሚጠበቁ በርካታ ገቢዎች ከሚጠበቀው በታች እየወረዱ በመምጣታቸው እንደ አገር የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት ያለመቻሉ፣

ለወርቅ አቅራቢዎች የሚከፈለው ማበረታቻ ተወዳዳሪ ባለመሆኑ ለባንኩ መቅረብ የነበረበት ወርቅ በሕገወጥ መንገድ በኮንትሮባንድ ገበያ እንዲሸጥ ምክንያት መሆኑ በጥናት መረጋገጡ፣

ባህላዊ የወርቅ አምራቾችን/አቅራቢዎችን ለማበረታታት በስራ ላይ የዋለው ማበረታቻ የወርቅ አቅርቦት መጠንን ታሳቢ ያላደረገ በመሆኑ በአቅራቢዎች መካከል አስተዋጽኦን መሰረት ያደረገ ውድድር የማያበረታታ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

በመሆኑም፣ ለወርቅ አቅራቢዎች የተሻለ የዋጋ ማበረታቻ በመስጠት እና አቅርቦትን በማሻሻል ከውጭ ምንዛሪ ግኝት አኳያ ከባህላዊ የወርቅ ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ማሳደግ እንዲቻል በስራ ላይ ያለውን የወርቅ ዋጋ ማበረታቻ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የውስጥ አሰራር መመሪያ ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡

1. አንቀጽ 1: አጭር ርዕስ

ይህ ማሻሻያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወርቅ ግብይትን (ዋጋን) በተመለከተ የሚከተሉት የተሻሻለ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 3/2015 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. አንቀጽ 2: ማሻሻያ

የወርቅ መግዣያ ዋጋ የተደነገገበት መመሪያ ቁጥር 1/2014 አንቀጽ 2 ተሰርዞ ከ50 ግራም ጀምሮ ለባንኩ ወርቅ ለሚያቀርቡ አቅራቢዎች የዋጋ እርከንን (category) መሰረት በማድረግ ቀጥሎ እንደተጠቀሰው ጭማሪ ተደርጎ የወርቅ ግዥ ይፈጸማል፡፡

2.1 የአቅርቦት መጠን ከ50 ግራም እስከ 150 ግራም በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 35% ጭማሪ ተደርጎ ይገዛል»፡፡

2.2 የአቅርቦት መጠን ከ150.01-1000 ግራም በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 52% ጭማሪ በማድረግ የሚገዛ ይሆናል»፡፡

2.3 የአቅርቦት መጠን ከ1000.01-5000 ግራም በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 55% ጭማሪ በማድረግ ግዢ ይፈጸማል፡፡

2.4 የአቅርቦት መጠን ከ5000.01 ግራም በላይ በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 60% ጭማሪ በማድረግ የሚገዛ ይሆናል»፡፡

3. አንቀጽ 3፡ ተፈጻሚነት

ይህ ማሻሻያ ከሚያዝያ 30 ቀን 2015 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1. ------------------------------------

ስለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

2. ------------------------------------

ስለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ